አንድ ሀገር
አንድ ሕዝብ
አንድ ሰንደቅ ዓላማና
አንድ የጋራ ዕድል

ONE COUNTRY
ONE PEOPLE
ONE FLAG & ONE
COMMON DESTINY

# የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር
## ማዕከላዊ ኮሚቴ
## (ኢአአግማኮ)
## ETHIOPIAN UNITY PATRIOTS FRONT CENTRAL COMMITTEE
## (EUPFCC)

ልዩ እትም ቁጥር 03 ግንቦት 27 ቀን 1998

# አንድነት ኃይል ነው ልዩነት ፈንጅ ነው

ሀገራችን የገጠማትን ችግር ለማስወገድና የሕዝባችንን የስልጣን ባለቤትነት ለማረጋገጥ ሲበል በአለፉት 15 ዓመታት ውስጥ በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል። ይሁን እንጂ ተቃዋሚው ኃይል ከፀረ-ወያኔነት አቋም ያለፈ ራእይና በተግባር የተደገፈ ሁነኛ ሥራ ለማከናወን ባለመቻሉ ወያኔው የበለጠ እያበጠና ከስልጣን ሊያስወግድው ቀርቶ ሊያስደነግጠው የሚችል ኃይል አለመኖሩን እንዲገነዘብ አድርጎታል። ይህም ኢትዮጵያን ለማፈራረስ የነደፈውን አጀንዳ ፋታ አግኝቶና ጊዜ ገዝቶ እንደፈለገው እንዲፏልል ከመርዳቱም በላይ ፍፁም ወደለየለት አምባገነናዊነት ተሸጋግሮአል።

የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር (ኢአአግ) በተደጋጋሚና በተለያዩ ጊዜያቶች ለመተባበር ካደረገው ሙከራና ባወጣቸው ድርጅታዊ መግለጫዎች አበክሮ እንደገለፀው ተቃዋሚው ኃይል መሠረታዊ ጠላትነቱ ወያኔው መሆኑን በሚገባ ቢያውቅም ወያኔን ለመጣል በሚደረገው ትግል ወስጥ የተፈጠሩት የአካሄድ ልዩነቶች መሠረታዊ ችግሮች ነበሩ።

እነዚህን ልዩነቶች ቢያንስ በማጥበብ (በመቀነስ) ወደ አንድ የጋራ መስመር (አመለካከት) ለማምጣት የወሰደው ገዜም ቀላል አልነበረም። በእርግጥ እነዚህ አሣሪ ችግሮች በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙለ ተፈትተዋል ባይበባልም ቢያንስ ቢያንስ አምባገነኑን የወያኔ አገዛዝ ለማስወገድ ያለው ብቸኛ አማራጭ የትጥቅ ትግል ብቻ መሆኑን የማመን ሕሳቤ ብዙዎቹ እየገበቻውና እየተረዱ መምጣታቸው እጅግ የሚያበረታታ ነው።

በዚህ መንፈስ መሠረት ተመሣሣይ የትግል ስልት ያላቸው ተቀዋሚ ኃይሎች ማለትም፤

1. የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር (ኢአአግ)

2. ታጠቅ የኢትዮትያ አንድነት ግንባር
3 የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር
4. የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር
የተባሉት ድርጅቶች ድል በአንድነት በተባለ ሕዝባዊና ሀገራዊ ማሕበር አማካኝነት ሲ.ው.ዲ.ን (እስኮትልም) ከግንቦት 18 ቀን እስከ ግንቦት 19 ቀን 1998 በተከሄደ የጋራ ስብሰባና ውይይት መሠረት የኢትዮጵያ አርበኞች ብሔራዊ አንድነት ሐይል በሚል ስያሜ የማጠራ ሕብረት መስርተዋል።

እነዚህ ተቃዋሚ ኃይሎች የየራሣቸውን የድርጅት ሕልውና በባለቤትነት እንደያዙ ሕብረት የፈጠሩ ቢሆንም የሕብረቱ መፈጠር ፤
1ኛ/ በመካከለቸው ያለውን ጥርጣሬ አስወግዶ መተማመንን ያዳብራል።
2ኛ/ የእርስ በእርስ መደነቃቀፍንና መጠላለፍን ያስወግዳል
3ና/ የጋራ መደጋፍንና የመረጃ ልውውጥን ያጠናክራል
4ኛ/ እነዚህ ሁኔነታዎች በሚፈጥሩትና በሚያገኙት ወጤት ላይ ተመስርቶ ደግሞ ከሕብረት ወደ ውሕደት ያሸጋግራል።

የሕብረቱ መመስረት በራሱ ግብ ባይሆንም ቢያንስ ቢያንስ ከእኛ ጀርባ የነበሩትን የየራሣችን ችግሮች በማስወገድ በጋራ መንቀሣቀስ መጀመራችን የሚያመላክት በመሆኑ በጐ ጅምር ነው ብለን እናምናለን። ምክንያቱም አንድነት ሐይል ነው ልዩነት ፈንጅ ነውና ይህ ጅምርም ሆነ ትግሉ ከየአቅጣጫው መጠናከር ይኖርበታል።

እኛ የምንከፍለው የእያንዳንዳችን የሕይወት መስዋእትነት የብዘ ሚሊዮን ወገኖቻችን ሕይወት የሚጠብቅና የሚለውጥ በመሆኑ ትግሉ ከጊዜም ጋር ጭምር ነው። የተግባር ሰዎች እንሁን ለሕዝባችን ትንሽ ካሣየነው ዛሬም ከእኛ ጋር ነው ለመሆንም ዝግጁ ነው። ሞቶም አሣይቶናል። ጆሮውን አቅንቶ መግቢያ በሩን ከፍቶ እየጠበቀን ነው።

በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የምትገኙ የኢትዮጵያ አንነደነት አርበኞች ግንባር አባላትም ለግንባሩዓላማዎች ስኬት በየአቅጣጫው የጀመራችሁትን ፀረ-ወያኔ የአርበኝነት ትግል አጠናክራችሁ እንድትቀጥሉ በአክብሮ እንገልፃለን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር
ሰልፍ የጀግና ድል የእግዚአብሔር ነው
የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር